..ትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
..ሳይንስና ከፍተኛ ትምህርት ሚኒስቴር
ደብረ ማርቆስ ዩኒቨርስቲ

The Federal Democratic Republic of Ethiopia
Ministry of science &hiegher Education
Debre Markos University

# የጨረታ ማስታወቂያ

*ደ/ማ/ዩ ብ/ግ/ጨ/38/2013*

የደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ በ2013 የበጀት ዓመት ከመንግስት በተመደበለት በጀት የበር መስኮት እና ተየያዥ ጥገና እቃወች ግዥ በግልጽ ጫረታ አወዳድሮ መፈፀም ይፈልጋል፡፡ ስለሆነም በጨረታው መሳተፍ የሚችሉ ከዚህ በታች የተገለጹትን ማለትም፦

1. በዘመኑ እና በዘርፉ የታደሰ የንግድ ስራ ፈቃድ እና የግብር ከፋይነት የምስክር ወረቀት ማቅረብ የሚችሉ እና የተጨማሪ እሴት ታክስ ተመዝጋቢነት ማስረጃ ማቅረብ የሚችሉ፤
2. ለጨረታ ማስከበሪያ የሚሆን 25,000 /ሀያ አምስት ሽህ ብር/በባንክ በተረጋገጠ ሲፒኦ ወይም በሁኔታ ላይ ያልተመሰረተ የባንክ ዋስትና በደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ ስም አሰርቶ ማቅረብ የሚችል ወይም በጥቃቅን የተደራጁ ከአደራጃቸው የመንግስት መ/ቤት ከላይ የተገለጸውን የገንዘብ መጠን የሚገልጽ የዋስትና ደብዳቤ በደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ ስም በማሰራት ማቅረብ የሚችሉ፡፡
3. ከላይ የተዘረዘሩትን መስፈርቶች የሚያሟሉ ተጫራቾች ሁሉ የጨረታ ዶክመንቱን ደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ አስተዳደር ህንፃ ቁጥር 27 ቢሮ ቁጥር 10 ወይንም አዲስ አበባ 4 ኪሎ ከቅድስት ማሪያም ቤ/ክርስቲያን ወረድ ብሎ ሮሚና ካፌ ላይ 1ኛ ፎቅ ቢሮ ቁጥር 7 ከሚገኘው ቢሮአችን ማስታወቂያው በአዲስ ዘመን ከወጣበት ቀን ጀምሮ ለ 15 ተከታታይ ቀናት የማይመለስ ብር 200.00/ሁለት መቶ ብር / በመክፈል መግዛት ይችላሉ፡፡
4. የጨረታውን ዶክመንት አስተማማኝ በሆነ ማጣበቂያ በታሸገ ፖስታ በማድረግና በፖስታ ላይ የአሰሪ መስሪያ ቤቱንና የድርጅቱን መሉ ስምና አድራሻ በመጻፍ ፊርማና ማህተም በማድረግ ማቅረብ አለባቸው፡፡
5. የጨረታውን ፋይናንሻያል ዶክመንት እንዲሁም የጫራታ ማስከበሪያውን ለየብቻ አስተማማኝ በሆነ ማጣበቂያ በታሸገ ፓስታ በማድርግ በተጠቃለለ እንድ ፓስታ በማሸግ ማቅርብ ይኖርባቸዋል፡፡
6. አሸናፊው ድርጅት አሸናፊነቱ በተገለፀለት ከ7 ተከታታይ የስራ ቀናት በኋላ ከ8ኛ ቀን ጀምሮ በተከታታይ 8 የስራ ቀናት ውስጥ በግንባር ቀርቦ አሸናፊ የሆነበትን ጠቅላላ ዋጋ 10% የውል ማስከበሪያ በማስያዝ ውል መያዝ የሚችል መሆን አለበት፡፡
7. ተወዳዳሪዎች የጨረታ ሰነዱን በአግባቡ በመሙላትና በማሸግ ጨረታው በጋዜጣ ከወጣበት ቀን ጀምሮ ከተከታታይ 15 ቀናት በኋላ በ16ኛው ቀን ከጥዋቱ 3፡59 ድረስ ደብረ-ማርቆስ ዩኒቨርስቲ **ህንፃ ቁጥር 27 ቢሮ ቁጥር** 10 ድርስ በመቅረብ በተዘጋጅው ሳጥን ውስጥ ማስገባት ሲኖርባቸው ጨረታው በዚሁ እለት ከጠዋቱ 3፡59 ሰዓት ላይ ተዘግቶ ተጫራቾች ወይም ህጋዊ ወኪሎቻቸው በተገኙበት 4:30 ይከፈታል፡፡ ነገር ግን በካላንደር የተዘጋ ከሆነ በሚቀጥለው የስራ ቀን ይሆናል ፡፡

8 በጨረታው መክፈቻ እለት ተጫራቾች መገኘት ካልቻሉ መስፈርቱን እስካሟሉ ድረስ በጨረታው ላይ ያልተገኙ ተጫራቾችን ፖስታ ጨምሮ በእለቱ ይከፈታል፡፡

የበለጠ መረጃ ለማግኘት በስልክ ቁጥር 058 771 66 91 ደውለው መጠየቅ ይችላሉ፡፡

*ዩኒቨርሲቲው ጨራታውን በከፊልም ሆነ ሙሉ በሙሉ የመሰረዝ መብቱ የተጠበቀ ነው ፡፡*

*ደብረማርቆስ ዩኒቨርሲቲ*

☎ 0587716691 ✉ 269 2M



Debre Markos University Procurement Administration Process No 1